ኢሰመጉ

EHRCO

# የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ
# ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

**ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው።**

**EHRCO stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.**

## በወቅታዊ የሀገራችን ሁኔታ ላይ ከኢሰመጉ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

**ሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም**

በመጋቢት ወር 2010 ዓ.ም. ገዢው ፓርቲ የአመራር ለውጥ ማድረጉን ተከትሎ በጠቅላይ ሚኒስትርነት የተሾሙት ዶ/ር ዐብይ አህመድ በበዓለ ሲመታቸው ወቅት ባደረጉት ንግግር ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መስዋዕትነት ለከፈሉ ዜጐች ያላቸውን ክብር መግለፃቸውና ስለደረሰባቸውም እንግልት ይቅርታ መጠየቃቸው፤ ዴሞክራሲ ለሀገሪቱ የህልውና ጉዳይ መሆኑን መግለፃቸው ይታወሳል። ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፣ የመደራጀት እና የመሰብሰብ ነፃነትን የተመለከቱ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊከበሩ እንደሚገባ ለዜጐች የሰጡት ቃል ላለፉት በርካታ አስርት አመታት የተለየ ሃሳብን በማንፀባረቃቸዉ ብቻ እስርና እንግልት ሲደርስባቸው የቆዩ ዜጎቻችንን የጉዳት ስሜት ያከመ ብቻ ሳይሆን ለሃገሪቱ መፃዒ ዘመን ተስፋ ፈንጣቂ ነበር።

አዲሱ የመንግስት አስተዳደር በተከታታይ የወሰዳቸው አዎንታዊ እርምጃዎች በሽብርተኝነት ተከሰው የነበሩ ግለሰቦች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲለቀቁ ያደረገ፤ በዉጪ አገር በትጥቅ ትግል ጭምር ሲንቀሣቀሱ የነበሩ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደ ሃገር ተመልሰው በሠላማዊ የፖለቲካ ትግል እንዲንቀሳቀሱ የጋበዘ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ያበረታታ እና መድረኮችን የከፈተ፤ በውስን ደረጃም ቢሆን ላለፉት አመታት በሃገራችን ለተፈፀሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ስር ለሰደዱ የሙስና ወንጀሎች ተጠያቂነትን ለማስፈን የተደረገው ጅምር ጥረት ዜጐች በመንግስት ላይ ከፍተኛ እምነትን እንዲያሳድሩ ያደረገ መሆኑ የማይካድ ነው። የዲሞክራሲ ተቋማትን በመገንባት ረገድም የተሄደዉ ርቀት እጅግ የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ በቅርቡም በብቃታቸዉ እጅግ የተመሠከረላቸዉ አዲስ የሰብዓዊ መብት ኮምሽን ኮሚሽነር መሾማቸዉ ድርጅታችን በከፍተኛ አድናቆት የሚመለከተዉ ነዉ። ድርጅታችን እነዚህን በመንግስት በኩል የተደረጉትን መልካም እርምጃዎች በሙሉ ልብ በማድነቅ እና እየተደረጉ ያሉ መልካም ጥረቶችን ለመደገፍ ያለውን ቁርጠኝነት በመግለፅ "ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር ሕዝብ ተስፋ የጣለበት አጋጣሚ እንዳይባክን!!" በሚል ርዕስ ሰኔ 22 ቀን 2010 ዓ.ም. የድጋፍ መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል።

ይሁን እንጂ በተለይ ከሰብአዊ መብቶች አያያዝ አንፃር ተጀምሮ የነበረው ተስፋ ሰጪ እርምጃ ከግዜ ወደ ግዜ ሲሸረሸር ቆይቶ ሁኔታዉ አሁን አሣሣቢ ደረጃ ደርሷል ብሎ ድርጅታችን ያምናል። በተለይም ዜጐች በፈለጉበት የሃገራቸው አካባቢ ኑሯቸውን የመመስረት እና በሰላም የመምራት መብቶቻቸውን ከፍተኛ ችግር ውስጥ የከተቱ እና በአጠቃላይ በአገሪቱ ወደ ሶስት ሚሊዮን የተጠጉ ዜጐች ከመኖሪያ ቀያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት የሆኑ በበርካታ የሃገራችን አካባቢዎች የሚነሱ ማንነትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች፤ በተለያዩ አካባቢዎች በቡድን የተደራጁ እና የታጠቁ ሃይሎች የሠላማዊ ዜጐችን ህይወት የቀጠፉና የሌሎችን የመሰብሰብ እና ሃሳብን የመግለፅ መብቶችን የተገዳደሩ ድርጊቶች ከአንድ አመት በፊት ኢሰመጉም ሆነ መላ ኢትዮጵያውያን ተስፋ ያደረጉበት መልካም አጋጣሚ እየባከነ ብቻ ሳይሆን ሃገሪቱን ወደ ከባድ ችግር እየመሩት እንደሆነ ድርጅታችን ያምናል። እነዚህ ድርጊቶች ከቁጥጥር ውጪ ወጥተው የዜጐችን ደህንነትና ሰብዓዊ መብቶች አደጋ ላይ ከመጣላቸው በፊት መንግስት ህጋዊ እና ተመጣጣኝ እርምጃዎችን በአጥፊዎች ላይ እንዲወስድ ኢሰመጉ በተለያዩ መግለጫዎቹ ሲወተውት ቆይቷል። አሁንም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኹነቶች ያላቸው ተፅዕኖ ከፍተኝነትና ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በሃገራችን የተከሰቱ ሁኔታዎች አስደንጋጭ እና በእጅጉ አሣሣቢ መሆናቸዉን ተከትሎ ኢሰመጉ ይህንን አስቸኳይ መግለጫ ለማውጣት ተገዷል።

1. **የሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በባሕር ዳር እና በአዲስ አበባ የተፈፀሙ ዘግናኝ ግድያዎችን እና በመንግስት እየተወሰዱ ያሉ ተከታታይ እርምጃዎችን በተመለከተ፡-**

ሰኔ 15/2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ እና በባህርዳር ከተሞች በሀገር መከላከያ እና በአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮች ላይ በተፈፀመ እና መንግስት "የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ነው" ብሎ በገለፀው ጥቃት ድርጊቱን አቀነባብረውታል ተብለው የተጠረጠሩትን የክልሉን የፀጥታ ሃላፊ ጨምሮ የስድስት የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ህይወት ማለፉ ይታወሳል። ኹነቱ የክልሉን ፀጥታ ከማደፍረሱም ባሻገር ህብረተሰቡ ድንጋጤ ውስጥ እንዲወድቅና በሀገሪቱ በአጠቃላይ ከፍተኛ ውጥረት እንዲነግስ አድርጓል። ሀገራችን በለውጥ ወቅት ናት በሚባልበት በዚህ ግዜ ውስጥ የተፈፀሙትን ግድያዎች ተከትሎ ከለውጡ በፊት የነበረውን የጭቁና እና አፈና ስርዓት በሚያስታውስ መልኩ መንግስት በተለይ ድርጊቶቹ በተፈፀሙባቸው ከተሞች እየወሰደ ያለው መጠነ-ሰፊ እስራት እየታየ ያለውን ተስፋ የሚያደበዝዝ ተግባር ነው። የእስራት ዘመቻው የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላትን እንዲሁም በመንግስት ላይ ጠንካራ ጥያቄዎችን የሚያነሱ ግለሰቦችን ማካተቱ የለውጥ ሂደቱን ወደኋላ እንዳይጐትተው ያሰጋል። በተለይም የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ)፣ የኢትዮጵያ ዜጐች ለማህበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)፣ እና የአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤት በመባል የሚታወቀው ስብስብ አባላትና ደጋፊዎች ናቸው በተባሉ ግለሰቦች ላይ በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች የተፈፀሙ እስራቶች ከፖለቲካ ተሳትፎአቸው እና ከሚያራምዱት አስተሳሰብ ጋር ተጣምሮ ሲታይ እያስከተለ ያለው ተፅዕኖ በፖለቲካ ፓርቲዎቹ እና በአዲስ አበባ ባለአደራ ምክር ቤቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ሃገራችን ኢትዮጵያ በጀመረችው አጠቃላይ የለውጥ ሂደት ላይ መሆኑ እጅጉን አሳሳቢ ያደርገዋል።

የፀረ ሽብር ህጉ መንግስት በራሱ የዜጐችን መብት እንደሚጥስና ተቃውሞን ለማፈን ይጠቀምበት የነበረ ህግ መሆኑን በገለፀበትና የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግም አዋጁን በማሻሻል በሂደት ላይ ባለበት ወቅት፤ በዚሁ በስፋት በተወገዘው እና ብዙ ጉዳት ባስከተለዉ ሕግ መሠረት በታሳሪዎች ላይ ምርመራ መጀመሩ ለውጡ ወደየት እያመራ ነው የሚል ስጋት እና ጥያቄን ያስነሳል።

2. **የኢንተርኔት አገልግሎት መዘጋትን በተመለከተ**

መንግስት ለዉጡ ከተጀመረ በኋላ በተለያዩ ጊዜያት መላ አገሪቱን የሸፈነ የኢንተርኔት አገልግሎትን የመዝጋት እርምጃ የወሰደ ሲሆን በቅርቡም ከአገር አቀፉ የ10ኛ እና 12ኛ ክፍል ፈተናዎች ጋር በተያያዘ እና በባሕር ዳር እና በአዲስ አበባ የተፈፀሙትን ግድያዎች ተከትሎ የጽሑፍ መልዕክት መለዋወጫና የኢንተርኔት አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ መቆየቱ ይታወቃል።

የኢንተርኔት አገልግሎት መሠረታዊ ከሆነዉ ሐሣብን በነፃነት ከመግለጽ መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ብቻ ሣይሆን ዛሬ አገልግሎቱ በራሱ በመብት ደረጃ ዕዉቅና እያገኘ ያለ ነዉ። በመሆኑም መንግስት በዘፈቀደ አገልግሎቱን የሚዘጋበት ሁኔታ ተቀባይነት የለዉም።ይልቁንም መንግስት የኢንተርኔት አገልግሎትን ሊዘጋ የሚችልበትን ሁኔታ የሚገዛ ግልጽ የሕግ ማዕቀፍ ሊኖር የሚገባ ሲሆን የሚወስደዉ እርምጃም ግልጽና ለመጠበቅ ከሚፈልገዉ የሕዝብ ጥቅም አንፃር ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል። ከዚህ አንፃር ከ10ኛ እና 12ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና ጋር ተያይዞ የተወሰደዉን እርምጃ በተመለከተ ድርጅታችን አስፈላጊ ነበር ብሎ የማያምን ሲሆን በአዲስ አበባና በባሕር ዳር የተፈፀመዉን አሰቃቂ ግድያ ተከትሎ የተወሰደዉን እርምጃ በተመለከተ ደግሞ ሁሉንም ዓይነት የኢንተርኔት አገልግሎት የተመለከተ እና በአገሪቷ ከጫፍ እስከጫፍ የተወሰደ እርምጃ የነበረ በመሆኑ ድርጅታችን እርምጃዉ ተመጣጣኝ አልነበረም ብሎ ያምናል። በመሆኑም መንግስት ከዚህ ዐይነቱ በጅምላ የኢንተርኔት አገልግሎትን የመዝጋት እርምጃው እንዲቆጠብ እና ከዚህ አንጻርም የመንግስትን ባህሪይ የሚገዛ የህግ ማዕቀፍ እንዲወጣ ድርጅታችን አበክሮ ይጠይቃል።

3. **የሲዳማ የክልልነት ጥያቄን በተመለከተ**

ባላፉት አመታት የሲዳማ ህዝብ የክልልነት ጥያቄ በተለያዩ ደረጃዎች እና ወቅቶች ሲነሱ መቆየታቸውና መንግስት ጥያቄውን እያጤነው መሆኑን መግለፁ ይታወሳል። መንግስት ለጥያቄው በተገቢው ፍጥነት ምላሽ ባለመስጠቱ በ11/11/11 የክልልነት እወጃን በተናጠል ለመውሰድ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በተወካዮች ምክር ቤት አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርታቸውን ባቀረቡበት ወቅት ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት የጠነከረ ምላሽ ውጥረቱን ይበልጥ አባብሶታል። በተመሳሳይም የክልልነት ጥያቄውን ከሚያስተባብሩ አካላት እየተሰጡ ያሉ ተከታታይ መግጫዎች እና ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ውጥረቱን ወደ የፀጥታ ስጋት ከፍ አድርጎታል። ይህም በሐዋሳ ከተማ እና በአቅራቢያ ከተሞች የሚኖሩ ዜጐችን በደህንነት ስጋት ላይ የጣለ ሲሆን የፀጥታ ስጋቱም ከፍ ወዳለ ደረጃ መድረሱን የሚያሣዩ ምልክቶች ተስተዉለዋል። በዚህ አጋጣሚ መንግስት፣ የሃገር ሽማግሌዎች፣ እንዲሁም ጥያቄውን የሚያስተባብሩ አካላት እና ምሁራን በፍጥነት የጋራ መፍትሔ በመፈለግ የደህንነት ስጋቱን እንዲያቃልሉ ወይም ዳግመኛ እንዲህ ዓይነቱ የደህንነት ስጋት እንዳይፈጠር እንዲሁም ጥያቄዉ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ብቻ እንዲፈታ በጋራ እንዲሰሩ ኢሰመጉ አጥብቆ ይጠይቃል።

4. **የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶች መግለጫዎችን በተመለከተ**

የገዢው ፓርቲ አባል ድርጅቶች መካከል ባለፉት ጥቂት ወራት ግልፅ የሆነ የሃሳብ እና የመስመር ልዩነቶች መኖራቸውና ውጥረቶች እንዳሉ በተለያዩ ግዜያት ይፋ ከሚያደርጓቸው መግለጫዎች መረዳት ይቻላል። በተለይም የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ(ህወሃት) እና አማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) በቅርቡ በየበኩላቸው የሰጧቸው መግለጫዎች በፓርቲዎቹ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ወደ ቃላት ጦርነት ከፍ ማለቱን የሚያሣዩ ከመሆኑም በላይ በክልሎቹ መስተዳድሮች መካከል ባለፈው አንድ

አመት የታየውን የመገዳደር ስሜት ወደ ግጭት እንዳይወስደው ያሰጋል። ሁለቱ ድርጅቶች በሰላማዊ እና በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ችግሮቻቸው እንዲፈቱ፤ በከረሩ መግለጫዎቻቸው የሁለቱን እህትማማች ህዝቦች ወደ ግጭት እንዳይገፉ፤ መንግስት ፓርቲዎቹ ችግሮቻቸውን በሠላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን መንገድ እንዲያመቻች እና የክልሎቹንም ሆነ የመላው ሃገሪቱን ነዋሪዎች ደህንነት የማስጠበቅ ስራውን እንዲወጣ ኢሰመጉ ይጠይቃል።

በአጠቃላይ መንግስት የህግ የበላይነትን ለማስፈን የነበረው ቁርጠኝነት በአፈፃፀም ብቃት ባለመደገፉ ባለፉት በርካታ ወራት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ሲፈፀሙ የቆዩት የሀገርን ሠላም የሚያደፈርሱ ህገወጥ ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲስፋፉ መንገድ መክፈቱ ታይቷል። ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. የተከሰተው አሳዛኝ ድርጊትም ሆነ የበርካታ ዜጐችን ህይወት የቀጠፉ ግጭቶችና ጥቃቶች፤ እያደጉ በመጡ ትንንሽ በሚመስሉና በወቅቱም በህግ አግባብ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገባቸው ችግሮች ሳይታረሙ በመቆየታቸው ምክንያት የተከሰቱ መሆኑን ኢሰመጉ ያምናል። ሃገሪቱን ለማረጋጋትና የዜጐችን ሰላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስጠበቅ በመላው ሃገሪቱ የህግ የበላይነትን ማስፈን የሚኖረው አስተዋፅዖ የማይተካ መሆኑን ኢሰመጉ ይረዳል። ከዚህ ድርጊት ጋር በተያያዘም ሆነ በሌሎች ህገወጥ ድርጊቶች ላይ ተሳትፎ አድርገዋል ተብለው በተጠረጠሩና የማያሻማ ማስረጃ በተገኘባቸው ግለሰቦች ላይ የሚወሰዱ ህጋዊ እርምጃዎች ተገቢነት አጠያያቂ አይደለም።

ይሁን እንጂ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድኖች እና ስብስቦች ላይ ያነጣጠሩ ናቸዉ የሚል ዕምነት መፈጠሩ፣ጥቂት የማይባሉ ታሳሪዎችም ፍርድ ቤት አለመቅረባቸው፣ እንዲሁም በባህርዳር እና በአዲስ አበባ የተፈፀሙትን አሰቃቂ ግድያዎች ተከትሎ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ታስረው የሚገኙ የባለአደራ ምክር ቤቱ የአመራር አባላትን ጨምሮ 6 ተጠርጣሪዎች ኢሰብዓዊ በሆነ መንገድ በጨለማ ቤት ውስጥ መታሰራቸውና በቤተሰብ የመጐብኘት መብታቸው መነፈጉ፤ የመንግስትን እርምጃ ከህግ ማስከበር ባሻገር በከተማ አስተዳደሩ ላይ በሚያነሱት ተቃውሞ ምክንያት እንዳይሆን ጥርጣሬን ፈጥሯል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ኢሰመጉ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ያቀረበው የመረጃ ጥያቄ ይህ መግለጫ ይፋ እስከሚሆን ድረስ ምላሽ አላገኘም። ኢሰመጉ ከአብን፣ ከኦፌኮ፣ ከኢዜማ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ከባለአደራ ምክር ቤቱ ባሰባሰበው መረጃ መሠረት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ አባሎቻቸው እና በተለያዩ የስልጣን እርከኖች ላይ የሚገኙ አመራሮቻቸው በሰኔ 15ቱ ድርጊት "በሴራው ተሳታፊ ነበራችሁ" በሚል ምክንያትና ከፖለቲካ ተሳትፎኣቸው ጋር በተያያዘ መታሰራቸውን አረጋግጠዋል። ኢሰመጉ ከፓርቲዎቹ ባሰባሰባቸው መረጃዎች መሠረት አብን 66 አባላቱ፤ ኦፌኮ 30 የሚሆኑ የዞን እና የማዕከላዊ ኮሚቴ አመራሮቹ፤ ኢዜማ 6 አባላቱ መታሰራቸውን አረጋግጠዋል። ኢሰመጉ ከፓርቲዎቹ እና በተለያየ መንገድ ያሰባሰባቸው መረጃዎች መንግስት እየወሰደ ያለው እርምጃ የዜጐችን የተለየ አመለካከት የማራመድና በፈለጉት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የመሳተፍ ሕገ መንግስታዊ መብታቸውን የጣሰ መሆኑን ያመለክታሉ። በመሆኑም ህግን ለማስከበር የሚወስዳቸው እርምጃዎች ሁሉ ህግን መሰረት ያደረጉ፣ የተጠርጣሪዎችን ህገ መንግስታዊ መብቶች ያከበሩ፣ የህዝብን መረጃ የማግኘት መብት የጠበቁ መሆናቸውን እንዲያረጋግጥ ኢሰመጉ ይጠይቃል።

**ማጠቃለያ**

ባለፈው አንድ አመት በርካታ እና እጅግ አበረታች አዎንታዊ እርምጃዎች የመወሰዳቸውን ያህል በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የዜጐች በሠላም የመኖር፣ ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወርና በፈለጉበት የሃገሪቱ አካባቢ ኑሮን የመመስረት፣ ሃሳብን የመግለፅና የፈለጉትን የፖለቲካ አመለካከት የማራመድ መብቶች ሲጣሱ ቆይተዋል። ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች ኢትዮጵያን በሀገር ውስጥ ስደተኞች ቁጥር በአለም ቀዳሚ አድርገዋት ቆይተዋል። እነዚህና ሌሎች ችግሮች ተጀምሮ የነበረውን ሃገራዊ ለውጥ ማዳከም ብቻ ሳይሆን ሃገራችን አግኝታ የነበረዉን ክብርና ዝና በእጅጉ እየጎዱ ይገኛሉ።

አሁን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከመቼውም ግዜ በላይ በከፍተኛ የሠላም እጦት ስጋት ውስጥ እንደምትገኝ ይታወቃል። ከዚህ ስጋት ለመላቀቅም መንግስት ከመቼውም ግዜ በበለጠ እርጋታ እና የሃላፊነት ስሜት ህዝብን እና የሚመለከታቸው አካላትን ሁሉ ያሳተፈ መፍትሔ እንዲያፈላልግ ኢሰመጉ ይጠይቃል። በተለይም ሰላምን ያመጣሉ በሚል የተቋቋሙት የሰላምና እርቅ እንዲሁም የማንነት እና የድንበር ኮሚሽኖች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ ኢሰመጉ ይጠይቃል። ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ የሃገሪቱ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ተቆርቋሪዎች ሁሉ ለሀገር ሠላምና አንድነት የየበኩላቸውን አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል። በዚሁ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) የተጀመረው ለውጥ አቅጣጫውን እንዳይስት የሚጠበቅበትን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው።